# የአባተ ቤተ ሰብ ልማት ማህበር መተዳደሪያ ደንብ

**መግቢያ**

በማህበር የመደራጀታችን ምክኒያት የሆነው የአባታችን በጎ ሥራ ነው፡፡አባታችን አባተ መኒሶ ትወልዳቸው በኢትጵዮጵያ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ በሃዲያ ዞን በአዎሳ ቀበሌ ሲሆን በሕይወት በነበሩበት ዘመን ሰውን አፍዋሪ፣ዘመድ ወዳጅ፣መንፈሳዊ አገልጋይና ልማት ፈጣሪ ለማህበረ ሰቡ ቦጎ ሥራ የሚያበረክቱ ተወዳጅ ሽማሌና ቀበሌ አስተዳደር ነበሩ፡፡

እኛም ከአብራካቸው ተወልደን፣አድገን፣ተምረን በአገር ውስጥና በውጭ አገር ወንድና ሴት ልጆች እንገኛለን በመሆኑም ለመታሰቢያቸው የሳቸውን ራዕይ ለማስቀጠል በትውልድ አገራችን ማሕበረ ሰባችንና እራሳችንን ለመርዳት መደረጀት አስፈላጊ መሆኑን በማመን በራሳችን ውዴታ በ--ቀን በማህበር ተደራጅተናል፡፡ የማሕበሩ መሥራች አባሎች የሚከተለውን መተዳደሪ ደንብ መሥርተናል፡፡

አንቀጽ1 የማህበሩ ስም ና ትርጉም

1.1 ማህበሩ የአመ[‹amf] ልማት ማህበር ተብሎ ይጠራል

1.2 ትርጉሙ የአባተ መኒሶ ቤተሰብ ልማት ማለት ነው፡፡

አንቀጽ 2 አርማና አድራሻ

2.1 የማህበሩ ዓርማ ምልክት amf ይሆናል

2.2 የመህበሩ ቢሮ በሃዲያ ዞን ሆማኞ ከተማ ይሆናል

አንቀጽ 3 ግንኙነት

3.1 እንደ አስፈልጊነቱ በአየር መገናኘት

3.2 በአሰፈላጊ ቦታ በዓመት አንዴ ወይም ከዛ በላይ በአካል በመሰባሰብ መገናኘት

አንቀጽ 4 ዓላማና ግብ

ዓላማችን፤ የሟች አባታችን በጎ ሥራ መታሰቢያ በማድረግ የእርስ በእርስ ፍቅር ማጠናከር፣በመተባበር ምጣኔ ሀብታችንን ሌሎችንም በሚጠቅም መልክ በማሳደግ ከድህነት መላቀቅ ነዉ፡፡

ግባችን፤ ገንዘባችንን አዋጥተን ስራ ላይ በማዋል ትርፋማ መሆን ነው፡፡

አንቀጽ 5 አደረጃጀት

5.1 ጠቅላላ ጉባኤ በማህበሩ የተደራጁ ሁሉንም ያቅፋል

5.3 ማሕበሩ የሚተዳደረው በመረጠው ቦርድ ይሆናል

5.3 ቦርዱ አምስት አባላት ይሆኑታል እነሱም ሥራ መሪ፣ጸሐፊ፣ገንዘብና ንብረት ግምጃቤት፣ሂሳብ ክፍል ኃላፊ፣ አማካሪ ይሆናሉ የቦርድ አባላት ብዛት እንዳስፈላጊነቱ ይጨመራል

5.4 **የገንዘብ ምንጭ፥** የአባልት መዋጮና የተቀማጭ ትርፍ

5.5 የአባል ዕድሜ፤ የእድሜ ገደብ የለም

5.6 የአባልት መዋጮ፤ የአንድ ጊዜ መዋጮ ከብር 100 ያላነሰ ሆኖ የአባሉ አቅም በፈቀደ ጊዜ ሁሉ፤

5.7 በስራ አስኪያጅ ኮሚቴ አመራር የተዋጣዉ ገንዘብ ትርፋማ እንዲሆን የንቀሳቀሳል

5.8 የመዋጮ ዝርዝር ሪፖርት በየወሩ ይለቀቃል

5.9 በአመቱ መጨረሻ የሂሳብ ሪፖርት ይቀርባል፣ በታቅላላ ጉባኤ ይጸድቃል

5.10 የአመቱ የተጣራ ከፒታል ከጥሬ ገንዘብ ዉጭ ያለ ንብረት ከወጣባቸዉና ከገበያ ዋጋ ከሁለቱ የሚያንሰዉ ተወስዶ በተሰላዉ መሰረት ተሰልቶ አዋጭዎች በከፒታሉ ያላቸዉ ድርሻ ይታወቃል

5.11 ከዓባልነት መሰናብት፥ ዓባል ከልማቱ ዓባልነት ቢወጣ ከተሰላዉ ድርሻ ዉስጥ መቀነስ ያለበት ወጭ ካለ ተቀንሶ ይሰጣል፣ አባሉ ሲመለስ እንደ አዲስ እባል ይሆላል።

አንቀጽ 6 ስልጣን

6.1 የማህበሩ ቦርድ ተጠሪነቱ ለጠቅለለ ጉበኤ ይሆናል

6.2 አስተዳደር ኮምቴ ተጠሪነቱ ለቦርዱ ይሆናል

6.3 ይህ ማህበር ሲጀመር የቦርዱ አባላት እንደ አስደዳደር ኮሚቴ አባላትም ሆነዉ ያገለግላሉ

6.4 የስልጣን ዘመን በየአምስት አመት ይታደሳል

አንቀጽ 7 ሃላፊነት

7.1 የማህበሩ ጉበኤ

1. በአሰፈላጊ ጊዜ ሁሉ መሰብሰብ
2. ዘገባ ማዳመጥ
3. በቀረበ አጀንዳ ተወያየቶ ወሳኔ መስጠት
4. ቃለ ጉበኤ ማጽደቅ
5. ስለጣን መስጠትና መሻር

7.2 የቦርድ አስተዳደር ኮምቴ ሃላፊነት፤

1. አጀነዳ መቅረጽ
2. ቦርድንና ጉባኤ በመጥራት ማጽደቅ
3. ዘገባ ማቅረብና ማዳመጥ
4. የዘርፎችን ሥራ መገምገምና አመራር መስጠት
5. የቦርዱንና የጉበኤ ውሳኔ ማስፈጽም
6. የገንዘብና ንብረት አያያዝና አወጣጥ በጉባኤው ውሳኔ መሠርት መሆኑን ማረጋገጠጥ

7.3 የማህበሩ መሪ

1. የቤተሰብ ተጠሪና ሥራ አስከሃጅ ሆኖ ያገለግላል
2. የቦርድ ና የጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ ይሆናል
3. በስብሰባዎቹ የጸደቁ ውሳኔዎችን ያስተላልፋል
4. ከገንዘብና ንብረት ክፍል ሃላፊ ጋር በመሆን ባንክ እዲከፈት በደባዳቤና በባነክ ቼክ ላይ ይፈርማል
5. በሚመለከተው አካል በሃላፊነት ይከሰሳል: ይከሳል

7.4 ግምጃቤቱ ፣

1. የማህበሩን ጥሬ ገንዝብና ንባረት በአስፈላጊ ቦታና በባንክ በጥንቃቄ ማስቀመጥ
2. በጠቅላላ ጉባኤ፣ በቦርዱ ወይም በኮሚቴ በፀደቀዉ ዉሳኔ መሰረት ከመሪዉ ጋር በመነጋገር ወጪ መፈፀም
3. የባንክ ደብተር መያዝ
4. በሂሳብ ሹሙ በመታገዝ የገቢና ወጪ ሪፓርት ማቀረብ
5. ባንክን በተመለከተ ጉዳይ ላይ መፈረም

7.5 ጸሐፊ

1. ቃለ ጉባኤ መያዝ
2. የመህበሩ አባላት ቁጥርና ተሰትፎ መዝግቦ መያዝ
3. ጠቅላላ የማህበሩ መረጃ ፋይል አድረጎ ማሰቀመጥና በተፈለገ ጊዜ ማቅረብ

7.6 ሒሳብ ክፍል ኃላፊ

1. በበንክ አካውንትና ቼክ ከመሪው ወይም ከግምጃቤቱ ጋር በመሆን መፈረም
2. የመህበሩን አስተዳደርናየዘረፉን ገቢና ወጪ ለየባቻቸው ለይቶ ሂሳብ መሥራት
3. የያንዳንዱን ዘርፍ ገቢና ወጪ ሂሳብ ሪፖረት ማዘጋጀት

7.7 አማከሪ

1. 1 በኮምቴ አባል በመሆን በውይይት መሳተፍ

2. የኮሙቴ አከሄድ በቅርበት ሆኖ መከታተል
3. ገንቢ ምክር መስጠት
4. በውሳኔ ሃሳቦች ላይ ከሌሎች ኮምቴ ጋር በመሆነ መፈረም
5. ለየማህበሩ ሥራ ስኬት ከኮምቴወረ ጋር አብሮ መሥራት

አንቀጽ 8 የቦርድ አባላት

8.1 ፓ/ር ገ/ ወልድ፤ አባተየማህበሩ መሪ
8.2 አቶ አብሪሃም፤ ገንዘብና ንብረት ግምጃቤት
8.3 አቶ በየነ አባተ፤ ጸሐፊ
8.4 አቶ ትዕግስቱ አባተ፤ አማከሪ
8.5 አቶ ሊሬ አባተ፤ ሒሳብ ክፍል ኃላፊ
አንቀጽ 9 የአባልነት መብት
9.1 የአባተ ማኒሶ የዘር ሐረግ ያለወ ወንድም ሴትም፤ባልም ሚሰት ያጠቃልላል
9.2 ለአባልነቱ ብቁ ነኝ ያለ ሁሉ በራሱ ውዴታ ደንቡኑና ውስጠ ደንቡን አወቆ በውደደው ዘርፍ አባል ይሆናል፡፡

አንቀጽ 10 ተሳትፎ

10.1 ድንቡ በሚጠይቀው መሠረት አስተዋጽኦ ማድረግ
10.2 በአካል ወይም በውክልና ተገኝቶ ማገልገል

አንቀጽ11 ደንብ መሻሻል

11.1 ደንቡ አሰፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሙለተ ጉባኤ ውሳኔ ይሻሻላል
11.2 በየአመቱ ይገመገማል

አንቀጽ11 ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

መሥራች አባሎቹ ተስማምተው ከጸደቁበትና አውቅና ከገኘበት ከዛሬ ---ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አንቀጽ 12 የመሥራች አባል ስምና ፍርማ

| ተ ቁ | ስም | ፊርማ |
|---|---|---|
| 1 | | |
| 2 | | |
| 3 | | |
| 4 | | |
| 5 | | |
| 6 | | |
| 7 | | |
| 8 | | |
| 9 | | |
| 10 | | |
| 11 | | |
| 12 | | |
| 13 | | |
| 14 | | |
| 15 | | |
| 16 | | |
| 17 | | |
| 18 | | |
| 19 | | |
| 20 | | |

| | | |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |